# ኢትዮጵያ ሃገሬ.... የአዲስ አበባ ከንቲባ ታከለ ኡማ ውሳኔ – ቅድስት ግርማህ

July 12, 2020

ዛሬ በአዲስ አበባ ከንቲባ ታከለ ኡማ ውሳኔ ለአርቲስት ሃጫሉ ሁንዴሳ መታሰቢያ ይሆን ዘንድ ት/ቤት በስሙ እንደተሰየመለትና በመቀጠልም በሃይሌ ጋርመንት አካባቢ የሚገኘውን አደባባይ በሃጫሉ ስም ለመሰየም መርሃ ግብር መያዙ ሰማን። ለአርቲስቱ የሚመጥነዉ ማስታወሻ ማስቀመጥ ተገቢ እንደሆ ስላመንኩ እሰየው ብለናል።

ነገር ግን...

በነ አለምፀሃይ ወዳጆ አማካኝነት አዲስ አበባን የቀረቀረቻት የእቴጌ ጠሃይቱ መታሰብያ ሃውልት ለመስራት የተቀመጠን የመስራት ድንጋይ በቁሮ መንጋ ሲፈርስ ታከለ ኡማ መጀመሪያ የፈቀደውን ፕሮጀክት ከኔ እውቅና ውጭ የተሰራ ስራ ነው በማለትና ሽምጥጦ በመካድ ፕሮጀክቱ እንዲቆም ማድረጉን አስታውሶኝ ሁኔታው አግራሞትን ፈጥሮብኛል።

ሌላው ከዚህ ጋር በተያያዘ...

ሃገሩን በኢኮኖሚና በልማት ለማሳደግ የሙቀት መጠኑ ከ38-40 ዲግሪ ሳልሲየስ በሚደርስ ሃሩር በርሃ ላይ ለ7 አመታት እየተቃጠለ ሲሰራ የነበረው የልማት አርበኛ ኢንጂነር ስመኘው የግፍ ግድያና በመንግስታችን የተሰጠው ምላሽ ትዝ አለኝና አንዳች ነገር ውስጤን ሰንጎ ያዘኝ።




~~~~~
~~~~~

የ53 ዓመት ጎልማሳ የኢንጂነር ስመኘው ስም በህዝብ እውቅና እያገኘ የመጣው የአባይ ግድብ ፕሮጀክት ማኔጀር ሆኖ ሲሾም ይሁን እንጂ ስመኘው የግልግል ጊቤ አንድንና ሁለትን ግንባታዎችን በመገንባት በሃላፊነት የተወጣ መሪ መሃዲስ ነበር።
ኢንጂነሩ የጀመረውን ግድብ እውን ለማድረግ ትጋቱ ይገርመኝ ነበር። በግድቡላይ የነበረው መሻት የህዝብ ግንኙነት እስኪመስል ድረስ ሊጎበኙ ለሄዱ ሰዎች ስሜት ውስጥ ገብቶ ንግግር ሲያደርግ ምኞቱ ከፊቱ ይታይ ነበር።
~~~~
እንዲህ አይነቱ ከራሱና ከቤተሰቡ ሂዎት የሃገሩን ያስቀደመው ስመ ጥር መሪ መሃዲስ በአክራሪ ኦነጋዊያን በጭካኔ ሲገድል እንኳንስ አደባባይና ት/ቤት ሊሰየምለት ለረጅም ጊዜ ከመቃብሩ ላይ ድንጋይ የሚያስቀምጥለት አልነበረም። ጭካኔ ከተሞላበት አገዳደሉም በላይ የጠ/ሚንስትራችን "አንድ ኢንጂነር ስመኘው የሚባል ሰው ሞቶ ተገኝቷል" ብለው የተናገሩትን መስማት ቅስም ስባሪ ነበር።

ሃገራችን መቼ ይሆን በመርህ የምትመራው❓

ያሳዝናል!!
~~~~